# ካርል ማርክስና ምዕራባውያን

መስፍን ወልደ ማርያም

ታኅሣሥ 2002

የካርል ማርክስ የፖሊቲካ ፍልስፍና ሞተ ተብሎ ወደመቃብር ከገባ ሃያ ዓመት ሊሆነው ነው፤ ስለካርል ማርክስ በጻፍሁት ያልታተመ ጽሑፍ ‹‹በይሁዲነት ተወልዶ፣ በክርስቲያንነት አድጎ፣ በከሀዲነት የሞተ›› በማለት የተገነባበትን ሁኔታ ለመግለጽ ሞክሬ ነበር። ብዙዎች በደንብ የተረዱት ሰዎች ስለምዕራባውያን የካፒታሊስት ሥርዓት (ወይም በደርግ ዘመን የሰው በላው ሥርዓት ሲባል የነበረው) ያደረገውን ትንታኔ ያደንቁታል፤ በማርክስ ላይ ከባድ ነቀፌታ የሚሰነዘርበት በመተንበዩ ላይ ነው። ዋናው ትንቢት የካፒታሊስት ሥርዓት እያደገና እየሰፋ ሲሄድ በውስጡ በሚፈጠሩት ቅራኔዎች የተነሣ ብጥብጥ ወይም በደርግ ቋንቋ አብዮት የሚባለው ይከሰትና ወደሶሺያሊስት ሥርዓት ይለወጣል፤ የሶሺያሊስት ሥርዓትም ወደኮሚዩኒስት ሥርዓት ይለወጣል፤ የሚል ነው።

በእርግጥ ማርክስ እንዳሰበው የካፒታሊስቱ ሥርዓት ደረቅና እስቲሰበር የሚጠብቅ አልሆነም በአዳዲስ ሁኔታዎች አዳዲስ መፍትሔዎችን እየፈጠረ ራሱን ሲያራምድ ቆይቷል፤ ባሕርዩን ባይለውጥም መልኩን እየለዋወጠ ማርክስ በገመተው ፍጥነት ወደአስከፊ ውስጣዊ ቅራኔዎች አልገባም፤ ምልክቶች ግን ነበሩ፤ ለምሳሌ የአሜሪካ ፋብሪካዎች እየተዘጉ የአሜሪካ ባለሀብቶች ወደእስያና ወደላቲን አሜሪካ አገሮች እየሄዱ ፋብሪካዎችን ሲያቋቁሙ ማርክስ ካፒታል (ሀብት) አገር የለውም ያለውን እያረጋገጡ ነበሩ። የእስያና የላቲን አሜሪካ አገሮች በምዕራባውያን የእውቀት ጥበብና ገንዘብ እንዲለሙና እንዲከብሩ ለማድረግ ሲረባረቡ አትኩሮታቸው ወደነሱ ኪስ የሚገባው ገንዘብ ላይ እንጂ በያገሩም ሆነ በዓለም ደረጃ የሚያስከትለውን ቀውስ ለማሰብ ፍላጎቱም የነበራቸው አይመስልም፤ ዓለም-አቀፍ ገበያ ብለውም የሦስተኛውን ዓለም አምባገነኖች እያሰለፉ ሲያባብሉና ሲያስገድዱ ቆይተዋል፤ በዚህም ምክንያት ብዙዎቹ የምዕራብ አገሮች በብዙ ሸቀጦች፣ በተለይ በልብስ፣ በጫማ፣ ቀጥሎም በራድዮን፣ በተለያዩ ቁሳቁሶች፣ በልጆች መጫወቻዎች ---- እያለ በመኪናና በኮምፒዩተሮችም ከአምራችነት ወደሸማችነት ተሸጋገሩ፤ በሦስተኛው ዓለም ሕዝብ ርካሽ ጉልበት እያተረፉ የተንደላቀቀ ኑሮ ለመዱ፤ እርስበርሳቸው ባለው ፉክክር ወዳጅንና ጠላትን መለየት አቃታቸው፤ እነሱን ለከፍተኛ የእድገት ደረጃ ያበቃቸውን የእኩልነት፣ የነጻነት፣ የፍትሕና የሕግ የበላይነት ረሱት፤ በሥልጣን መባለግ፣ ማጭበርበር፣ ከማጅራት መችነት ያላነሰ ወንበዴነትና ዝርፊያ ባህላቸው ሆነ፤ ዋጋ ያላቸው ማዕድናት ያላቸውን አገሮች ሁሉ በግድም ይሁን በውድ በቁጥጥራቸው ስር አዋሉ፤ በብድር የኑሮ ዘዴ የውሸት መንደላቀቅ አሰከራቸው፤ ቀስ በቀስም ሌሎች ደሀ ሕዝቦች የነሱን ጦርነቶች እንዲዋጉላቸውና እነሱን እሳቱ እንዳይነካቸው ሁኔታዎችን አመቻቹ።

በዚህ ዓመት ጉድ ፈላባቸው፤ የገንዘብ ንግዳቸው ተንገዳግዶ ወደቀ፤ ወይም እነሱ እነደሚሉት ቀልጦ ተንጠባጠበ፤ ብዙ ሀብታሞች የተባሉ ሞላጮች

በአውሮፓም፣ በአሜሪካም ተያዙ፤ በዚህ ሳምንት እንኳን አንድ ሞላጫ ሀብታም **ከሀምሳ ቢልዮን** (ሚልዮን አይደለም ቢልዮን) ዶላር በላይ ማጭበርበሩ ታወቀ፤ ሃምሳ ቢልዮን ዶላር ማለት በግርድፉ አምስት መቶ ቢልዮን የኢትዮጰያ ብር ይሆናል፤ አሥር ጊዜ ግድም የኢትዮጵያን የዘንድሮ ዓመት በጀት ያህላል ማለት ነው! ባንኮችና የኢንሹራንስ ኩባንያዎች ተራቆቱ፤ በብድር የተሠሩና የተገዙ ቤቶች ሁሉ ከፋይ በማጣታቸው በአበዳሪው ባንክ ተያዙ፤ ባንኮቹም ራሳቸው እየከሰሩ የመንግሥትን እርዳታ የሚጠይቁ ሆኑ፤ የመኪና ፋብሪካዎች ወደኪሳራ በመጠጋታቸው የመንግሥትን ድጋፍ ጠየቁ፤ አሜሪካ የቻይና ባለዕዳ ሆነ። ቻይናን ጨምሮ ብዙ የሦስተኛ ዓለም አገሮች በዓለም-አቀፍ ገበያ በተባለው ላይ ተስፋቸውን መሥርተው የገነቧቸውን ፋብሪካዎች መዝጋት ተገደዱ፤ በያለበት ብዙ ሠራተኞች ከሥራቸው እየተፈናቀሉ በቤታቸው እንዲቀመጡ ግዴታ ሆነ፤ የሕዝብ ቁጣ በአስከፊ መልኩ እየተገለጸ ነው። በብዙ የበለጸጉ አገሮች የንግዱና ፋብሪካው ፊታውራሪዎች በግፍና በገፍ ሲዘርፉ ኖረው ዛሬ በዓመት አንድ ዶላር ደመወዝ ብቻ እያገኙ ለመሥራት ፈቃደኞች መሆናቸውን እየገለጹ ናቸው።

ይህ ሁሉ የሚያሳየው ማርክስ እንዳለው የካፒታሊስት ሥርዓት በውስጡ ብዙ ቅራኔዎችን የያዘ መሆኑን ነው፤ ዛሬ በአውሮፓና በአሜሪካ መንግሥት የሕዝብን ገንዘብ እያወጣ የግል የንግድና የፋብሪካ ድርጅቶችን በተለያየ መንገድ መደጎሙ የውስጥ ቅራኔዎቹ የመጨረሻ መግለጫ ነው። ለምን ተብሎ ነው ሲበዘበዝ የኖረ ሕዝብ አሁን በዝባዡ ሲጨነቅ ለእርዳታ የራሱን ኑሮ እየጎዳ እንዲደጉመው የሚደረገው? ጨው ለራስህ ስትል ጣፍጥ፤ አለዚያ ድንጋይ ነው ብለው ይጥሉሃል፤ ትክክለኛ መመሪያ የሚሆነው አሁን ነበር፤ ምዕራባውያን የስድ ገበያ እምነታቸውን ለመጠበቅ ድንጋዩን ጨው ለማድረግ እየጣሩ ይመስላሉ፤ ከአሁን በኋላ ግን መሪዎቹ ለማታለል ቢፈልጉም ሕዝቡ የሚታለል አይመስልም። እውነቱ ፍጥጥ ብሎ ሲታይ እንኳን ሌላው ሲአይኤም ይጨክናል፤መጨካከን እየመጣ ነው፤ ኋላቀር የነዳጅ ዘይት አምራቾች ነገሩ ገና አልገባቸውም፤ ዓለምን በቤንዚን ብር ለመንዳት የነበራቸው ሕልም እያከተመ ነው፤ ዓለም ተለውጧል፤ ቤንዚን ከጥቂት ወራት በፊት በበርሚል ወደመቶ ሃምሳ ዶላር ደርሶ ነበር፤ ዛሬ አሽቆልቁሎ ወደሠላሳ አምስት ብር እንዘጭ ብሏል።

ለሀብታም አገሮችም ቢሆን ከአሁን ወዲያ በቀኝ እጅ እየዘረፉ በግራ እጅ እየቆነጠሩ የሦስተኛው ዓለም አሽከሮቻቸውን የሚደጉሙበትና የሕዝብን ቁጣ ማስታገሻ የሚሆን የብስኩት እርዳታ የሚሰጡበት አቅም እያነሰ ወይም ጭራሹኑ እየጠፋ ሊሄድ ወደሚችልበት ደረጃ ላይ የደረስን ይመስላል። ቀበቶን ጠበቅ አድርጎ በሰለሉ የገዛ እግሮች ላይ መቆም ግዴታ ሊሆን ነው፤ ምናልባት ግዴታው ያቀራርበንና ያፋቅረን፣ ያሳድገንም ይሆናል፤ ካወቅንበት።